## ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)

ግንቦት 16፣ 2004 ዓም

# የህወሃት/ኢ.ህአዴግ ድንበር ዘለል ወረራ በደቡብ ሱዳን!!

አቶ መለስ የሚመሩት የህወሃት/ኢ.ህአዴግ አገዛዝ ካደገበት ባህሪውና ፍጥረቱ የተነሳ በመላው አገራችን ላይ የዘረጋው የአፈና ተግባር እጅግ ከፍተኛ የሆነ የኢትዮጵያን አንጡራ ኃብት የበላ ስለመሆኑ ያለማቋረጥ ስንናገረው የነበረ፣ ሌሎችም የሚሉት፣ በርካቶች የስርዓቱን ገበና የሚያውቁት የሚመሰክሩት ሃቅ ነው።

ይህ ድርጅት ቀስ በቀስ የቤተሰብ ቅርፅ እንዲይዝ ከተደረገ በኋላ ስርዓቱ የስለላ መዋቅሩን በማስፋት አውሮፓ፣ አሜሪካ፣ አፍሪካ በተለይም ጎረቤት አገሮች ውስጥ የስለላ ሰራተኞችና የስለላ መረብ በማደራጀት እየፈፀማቸው ያለው ተግባራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ነው። በሱዳን፣ በኬኒያ፣ በዩጋንዳ … ተፈጽመዋል ከተባሉት ሁሉ እጅግ የከረረ፣ ገሃድ የወጣና የአንድን ሉዓላዊ አገር በመዳፈር ተፈጸመ ስለተባለው ጉዳይና በጉዳዩ ላይ ያለንን ስጋት ማሳወቅ አግባብ መስሎ ታይቶናል። ጉዳዩ በአዲሲቷ አገር ደቡብ ሱዳን የተከናወነ ነው።

**የአኙዋክ የፍትሕ ምክርቤት** (Anuak Justice Council - AJC) **ያሰራጨው መግለጫና፣** South Sudan News Agency **ትልቁና ዋናው የደቡብ ሱዳን የዜና አገልግሎት በፊት ለፊት ገጹ ያስተጋባው ዜና የጋራ ንቅናቄያችን በእጅጉ ያሳሰበ ሆኗል።** ዜናዎቹ ቀደም ባሉት ጊዜያት ደጋግመን ስንለው የነበረው የህወሃት/ኢ.ህአዴግ ጣልቃ ገብነትና ስርዓት መልቀቅ ከምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ የሚያሳዩ ሆነው አግኝተናቸዋል።

ህወሃት/ኢ.ህአዴግ በሰላም ማስከበርና በተለያዩ የፖለቲካ ሽፋኖች የአቻ ጎረቤት አገሮችን ሉዓላዊ ክልል በመጣስ የሚፈፅመውና እየፈፀመ ያለው ተግባር ከልክ ያለፈበት ደረጃ መድረሱን የሚያረጋግጠው የዛሬው መነሻችን "ወደፊት ዝርዝር ይቀርብበታል" በሚል የአኙዋክ የፍትሕ ም/ቤት ያወጣውን መግለጫ የሚንተራስ ነው።

**ሜይ 23 ቀን 2012 ምክርቤቱ አያቶቻቸው፣ አባቶቻቸው፣ ልጆቻቸው እንዲሁም አሁን በምክርቤቱ ውስጥ ያሉ አኙዋኮች ለአገራቸው የከፈሉት መሰዋዕትነት ከቶውን ሊረሳና ቸል ሊባል የማይችል መሆኑን ጠቅሶ ለደቡብ ሱዳን ፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪርና በመንግሥታቸው ውስጥ ላሉ ሁሉ የተላለፈው መልዕክት ጠንካራ ነው።** በደምና በአጥንት ብሎም በመስዋዕትነት የተቆራኘውን ግንኙነት በማስታወስ የወጣው መግለጫ መነሻው በደቡብ ሱዳን ፖሊስ በቁጥጥር ስር ውለዋል የተባሉትን የአኙዋክ ብሄር አባላትን አስመልክቶ ጥንቃቄ እንዲደረግ ያሳስባል፤ ይጠይቃል፤ ይሟገታል።



የፎቶ ምንጭ፡ የአኙዋክ የፍትሕ ምክርቤት

ድርጊቱ የተፈፀመው የህወሃት/ኢ.ህአዴግ የስለላ ሰራተኞች የሆኑ ሁለት የአኙዋክ ተወላጆች ደቡብ ሱዳን ፖቻላ አስተዳደር አላሪ የስደተኞች ጣቢያ ዘልቀው እንዲገቡ ከተደረገ በኋላ ነው። መግለጫው እንደሚለው የስደተኞች ጣቢያው ከ2003 የጋምቤላ የጅምላ ጭፍጨፋ የሸሹ በሺህ የሚቆጠሩ የአኙዋክ ብሔር አባላት የሚኖሩበት ነው። ህወሃት በካምፑ ውስጥ "ምን ይከናወናል?" በማለት እንዲሰልሉ ያስገባቸው ሰዎች ያለ ደቡብ ሱዳን ፈቃድና የጉዞ ሰነድ መሳሪያ በመታጠቅ የሰረጉ ናቸው። የፍትሕ ምክርቤቱ ዋና ጥያቄ ህወሃት/ኢ.ህአዴግ በአንድ ሉዓላዊ አገር ገብቶ ያሻውን የሚያደርገውና የዓለም አቀፍ የስደተኞችን ህግና የስደተኞች መጠለያ ክልል እየጣሰ እንደፈለገው የሚያደርገው በምን ስሌት ነው የሚል ነው፡፡ የጋራ ንቅናቄያችንም ይህንኑ ጭብጥ ይጋራል - ጥያቄውንም በአጽዕኖት ይጠይቃል፡፡

**ሁለቱ ሰላዮች የስደት ካምፑ ውስጥ ከደረሱ ከሁለት ቀን በኋላ የህወሃት የስለላ ኃይሎች የተካተቱበት በደቡብ ሱዳን ፖሊስና በጥቂት የአኙዋክ "ሽማቂዎች" መካከል በተካሄደ የተኩስ ልውውጥ አራት ተገድለዋል። ሁለቱን የአኙዋክ ብሔር አባላት የሆኑ የደህንነት ሰራተኞችን ጨምሮ ስድስት ሽማቂዎች በደቡብ**

**ሱዳን ፖሊስ ተይዘው ጁባ ባለው የህወሃት/ኢህአዴግ ኤምባሲ ወጪ በቀረበ ቻርተርድ ጀት ወደ ጁባ መወሰዳቸውን ያተተው መግለጫ፣ ቅዳሜ ቀን አስራ አንድ ተጠርጣሪ የአኙዋክ ሽማቂዎች ቦማ በምትባል ቦታ መያዛቸውንና በተመሳሳይ ጁባ ያለው የህወሃት/ኢህአዴግ ኤምባሲ ወጪውን በመሸፈን በግል ጀት ወደ ጁባ እንዲጓጓዙ መደረጉን መግለጫው ምንጮቹን ጠቅሶ ዝግቧል።**

*አኙዋክ ፍትሕ ምክርቤት አንክሮ በመስጠት የገለፀውና በአንድ ሉዓላዊ አገር የውስጥ ጉዳይ ውስጥ በማን አብኝነት እንዳሻቸው የመዳከር ያህል አድርጎ ያቀረበው ጉዳይ በደቡብ ሱዳን መንግስት እጅ ያሉትን የአኙዋክ ብሄር አባላትን ለማፈንና ለመውሰድ በጓሮ ሲሰራ የነበረው "አስነዋሪ" ተግባር ነው። ምክርቤቱ የድርጊቱንም ህገወጥነትና ድንበር ዘለል ጣልቃ ገብነት ሲያወግዝ ለደቡብ ሱዳን መንግስትና ለፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪር ያስተላለፈው መልዕክት የዜግነት ጥያቄም በማንሳት ነው።*

**ጁባ ያለው የህወሃት /ኢህአዴግ ኤምባሲ ጥቂት የህዝብ ተመራጮችንና ሰራተኞችን በማባበል ወይም በመደለል አስራ ሰባቱን የአኙዋክ ብሄር አባላት ወደ ኢትዮጵያ ለመውሰድ ሁሉንም ሥራ አጠናቅቆ ነበር። የህወሃት/ኢህአዴግ የጁባ ኤምባሲና የደህንነቱ ሃይል ባቀነባበረው መሰረት ሰዎቹን ለመውሰድ የአየር ሃይል አውሮፕላን (ከኢትዮጵያ) በማስላክ ጁባ አውሮፕላን ማረፊያ እንዲደርስ ተደረገ። በሌላ በኩል በግል ጀት ሰዎቹ ካሉበት የስደተኛ ካምፕ ተጭነው እንዲመጡ የማመቻቸቱ ስራ ተጠናቆ ስለነበር፣ ሰዎቹ በሰንሰለት ታስረው ተላልፈው ወደሚሰጡበት አውሮፕላን ተጫኑ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ነበር የአኙዋክ ፍትሕ ምክርቤት በአካባቢው ከነበሩት ምንጮቹ መረጃ የደረሰው። መግለጫው እንደተቆመው በዚህ ቅፅበት ውስጥ የካውንስሉ አመራሮች ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኛ ጉዳይ ኮሚሽነር (UNHCR) ባለስልጣናት ጋር አስቸኳይ ንግግር አደረጉ።**

**የስደተኛ ኮሚሽን ባለስልጣናትም በደቡብ ሱዳን ለሚገኙት የራሳቸው ባልደረቦችና ከሱዳን መንግስት ባለስልጣናት ጋር ባደረጉት ንግግር ሰዎቹን ጭኖ ለመብረር ተዘጋጅቶ የነበረው የአየር ኃይል አውሮፕላን ከማኮብከቢያው ሳይነሳ ቀረ።**




**ከስድስት ሰዓታት ቆይታ በኋላ ባዶውን የተመለሰው አውሮፕላን**

*ከህወሃት የደህንነት ሃይሎች፣ ከጁባ ኤምባሲ፣ ከሱዳን የደህንነት ክፍሎች ጋር ሰዎቹን አስመልክቶ ክርክር ቢካሄድም ከስምምነት ላይ መድረስ አልተቻለም። እንደ መግለጫው ሰዎቹ ትክክለኛ ስደተኛ መሆናቸው እስኪታወቅ በማቆያ እንዲቆዩ ተደርጓል ካለ በኋላ መረጃው አስፈላጊ ለሚባሉት ክፍሎችና ለሱዳን ባለስልጣናት ባይደርስ ኖሮ ሰዎቹ ተላልፈው ተሰጥተው እንደነበር በሃዘኔታ ይገልጻል።*

**"እንዲህ ያለው ተግባር እንዴትና በማን ተፈፀመ፣ ከድርጊቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሊቀጡ ይገባል"** ሲል የሚጠይቀው የምክርቤቱ መግለጫ የሚጋራው የጋራ ንቅናቄያችን የስጋቱም ምንጭ የሆነው ህግና ስርዓትን የመጨፍለቅ አካሄድ አግባብ ባላቸው አካላትና በደቡብ ሱዳን መንግስት አማካይነት መላ ካልተበጀለት በሰዎቹ ላይ ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ከፍተኛ ሊሆን ስለሚችል ነው።

**ግርፋት፣ ግድያ፣ ማሰቃየት፣ እስርና አስገድዶ ማሳመን ልዩ መለያው የሆኑለት የአቶ መለስ አገዛዝ በዓለም ጎልቶ የሚታይበትን ሙስና ደቡብ ሱዳን ላይ እንዳያዛምት ከፍተኛ አትኩሮት መደረግ እንዳለበት የሚያስጠነቅቀው መግለጫ ፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪር ሁኔታው እንዲጣራ ትዕዛዝ እንዲሰጡ ጠይቋል።** በሌላ መልኩ ጥንቃቄና ስሌት በጎደለው ሁኔታ ህወሃትን መወዳጀት ለአዲሲቷ ደቡብ ሱዳን አደጋ እንደሚሆንባት ያሳሰበው መግለጫ የመለስ ወዳጅ የሆኑት አልበሽር ሁለት ሚሊዮን ለሚጠጉት የደቡብ ሱዳን ህዝቦች ግድያ ተጠያቂ እንደሆኑና አሁንም ቢሆን የደቡብ ሱዳን ስጋት መሆናቸውን አመልክቷል። አልበሺር አሁን ድረስ የደቡብ ሱዳን ህዝቦችን "ትንኝ" እያሉ እንደሚጠሩዋቸው ያሰመረው የአኙዋክ ፍትህ ምክርቤት፣ በኢትዮጵያና በደቡብ ሱዳን ለሚገኘው መላው የአኙዋክ ህዝብ ስጋት ከሆኑት ከአቶ መለስ ጋር የደቡብ ሱዳን መንግሥት እየፈጠረ ያለውን ህብረት ብሄራዊ ክብሩንና አገራዊ ዋጋውን አደጋ ላይ ሊጥለው እንደሚችል ያስጠነቅቃል። መለስና አልበሽር በቅርቡ "ስደተኞችን" በ"ወንጀለኛ" ሥም አሳልፎ የመስጠት ውል የተፈራረሙበትን አግባብ አመልክቷል።

**"ደቡብ ሱዳን በኢትዮጵያ ካሉትና በደቡብ ሱዳን ከሚገኘው የአኙዋክ ህዝብና መሬት ጋር ያላትን ዓይነት በደምና በሥጋ የተሳሰረ የድንበር ወሰነተኝነት ከትግራይ ክልል ጋር የለውም፡፡ ተጎራባችና ድንበርተኛ አገር አይደለም" ያለው የፍትሕ ምክርቤቱ፣ ስለምን ደቡብ ሱዳን ህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ የመንደርደሪያ ሜዳ ትሆናለች ሲል ይጠይቃል። አያይዞም "እኛ የአኝዋክ ብሄር አባላት ተላልፈን እንድንሰጥ አልነበረም ለደቡብ ሱዳን ነጻነት የደም ዋጋ የከፈልነው" ሲል የድርጊቱን አስከፊና አስነዋሪ አካሄድ አሳይቷል።**

ፖቻላ በብዛት የአኙዋክ ህዝብ የሚኖሩበት ምድር በመሆኑ በተደጋጋሚ የህወሃት የመረጃ ቡድን በስፍራው መረጃ ለማግኘት መቸገሩ ስጋቱን እንደጨመረበትና፣ በዚሁ ሳቢያ በጋምቤላ በተደጋጋሚ የደረሰው ጥፋት ከዚያ በመንደርደር የተፈጸመ ነው በሚል በርካታ ሰብአዊነት የጎደለው ተግባር የሌላን አገር ድንበር ዘልቆ በመግባት መፈፀሙን ያወሳው መግለጫ የደቡብ ሱዳን መንግስት ከምንም በላይ ጥበቃና ዋስትና እንዲሰጥ አስገንዝቧል።

የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) እንደ ሌላው ጊዜ ሁሉ በሰብዓዊነት መጓደል የሚደርሱ በደሎችን አጥብቆ ይኮንናል፤ ይታገላል። በዚሁ መሰረት ከህግ ውጪ በነዚህ ወገኖች ላይ ሊወሰድ የነበረውን ድርጊት አጥብቆ ይቃወማል። አግባብ ባለው መንገድ ሁሉ ፍትሕን ለማስፈን ይታገላል። **ከሁሉም በላይ ዜጎችን ጎረቤት አገር ድረስ በማሳደድ በህወሃት/ኢህአዴግ የሚፈፀመውን አፈና አጥብቆ ይጸየፋል፤ ተዋናዮቹም ያጋልጣል፤ ለፍርድ እንዲቀርቡም ያደርጋል።**

ከአገራቸውና ከሃብታቸው ተካፋይ እንዳይሆኑ የተፈረደባቸው ህዝቦች፣ በአገራቸው ሆነው ለመብታቸው ሲከራከሩ የሚገደሉና የሚታሰሩ ህዝቦች፣ በጅምላ የተጨፈጨፉ ህዝቦች፣ አሁንም እየታሰሩ፣ እየተደገሉ ያሉ ወገኖች በስደት አሉበት ድረስ በየአገሩ በመዟዟር የሚፈጸምባቸውን አፈና ከመቃወምና ከመታገል በላይ ታላቅ ተግባር የለም። ስለሆነም በመግለጫ እንደተባለው ለደቡብ ሱዳን መንግስትና ለአለም አቀፍ ተቋማት ተመሳሳይ መልዕክት እንዳለን ለመግለፅ እንወዳለን። ለአገራቸው ደቡብ ሱዳን ነፃነት ህይወታቸውን የሰዉ ወገኖቻችን በራሳቸው ወንድሞች ክህደት እንዳይፈፀምባቸው ጊዜያዊ ከለላ ብቻ ሳይሆን ዘላቂ ዋስትና በተፈጠሩበት ምድራቸው እንዲከበርላቸው ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

አኙዋኮችም ሆኑ ሌሎች የታገሉለት የአገራቸው የደቡብ ሱዳን ነጻነት ለጠላት ተላልፎ የሚያሰጣቸው መሆን የለበትምና ፕሬዚዳንት ሲልቫ ኪር ለህዝባቸው፣ ለአፍሪካና ለሰብዓዊነት ቅድሚያ ተምሳሌት እንዲሆኑ አበክረን እንጠይቃለን። **እነዚህ ወገኖቻችን በስውር ተይዘው የህወሃት/ኢህአዴግ የአፈና መዋቅር እጅ ከመውደቃቸው በፊት አስፈላጊውን ሁሉ በማድረግ ለታደጓቸው ሁሉ የጋራ ንቅናቄያችን ምስጋናው ከፍተኛ ነው። ጉዳዩን ከአኙዋክ የፍትሕ ምክርቤት ጋር በመሆን በቅርብ እንከታተላለን፡፡ አግባብ ካላቸው ዓለምአቀፍ አካላት ጋር በጋራ በመሥራት ጉዳዩን ዳር በማድረስ በወቅቱ ለሕዝባችን ይፋ እናደርጋለን፡፡**

## ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነትን (media@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

